የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፲፬
አዲስ አበባ—ጥር ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፬

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

8th Year No. 14
ADDIS ABABA–31st January, 2002

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፪፻፷፯/፲፱፻፺፬ ዓ.ም.
የእንስሳት በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ....................................................... ገጽ ፩ሺ፮፻፺፬

CONTENTS

Proclamation No. 267/2002
Animal Diseases Prevention and Control Proclamation ........................................... Page 1694

## አዋጅ ቁጥር ፪፻፷፯/፲፱፻፺፬
## የእንስሳት በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ

የሀገሪቱ የእንስሳት ሃብት ለእርሻ ተግባር፣ ለምግብነት፣ ለኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃ፣ ለውጭ ምንዛሬ ማስገኛ በጠቅላላው ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት መሠረት ከሆኑት ዋና ሃብቶች አንዱ መሆኑን በመገንዘብ፣

ከዚህ ሰፊ የእንስሳት ሃብት የሚገኘውን ጥቅም ለማሳደግ በቅድሚያ የእንስሳት በሽታዎችን በሚገባ መከላከልና መቆጣጠር ወሣኝ እየሆነ በመምጣቱ፣

ለዚህም ከውጭ ሀገር ወደ ሀገር ውስጥ፣ ከሀገር ውስጥ ወደ ውጭ እንዲሁም በሀገር ውስጥ ከቦታ ቦታ የእንስሳት፣ የእንስሳት ውጤቶችና ተዋጽኦዎች ዝውውር ሥርዓት በመዘርጋት የእንስሳት በሽታዎችን መቆጣጠር አስፈላጊ በመሆኑ፣

በአጠቃላይ የእንስሳት በሽታዎችን በመቆጣጠርና በዓለም አቀፍ ደረጃ የተደረሱትን የእንስሳት ጤና ስምምነቶች በመጠበቅ የእንስሳት፣ የእንስሳት ውጤቶችና ተዋጽኦዎችን ኤክስፖርት ንግድ ማስፋፋት አስፈላጊ በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ክፍል አንድ
### አጠቃላይ ድንጋጌዎች

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የእንስሳት በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣ አዋጅ ቁጥር ፪፻፷፯/፲፱፻፺፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

፩· "ሚኒስትር" ወይም "ሚኒስቴር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የግብርና ሚኒስትር ወይም ሚኒስቴር ነው፣

## *PROCLAMATION No. 267/2002*
## *A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE PREVENTION AND CONTROL OF ANIMAL DISEASES*

WHEREAS, taking into consideration that the country's livestock resource is a source of draft power for agriculture and source of food, raw materials for industries, foreign exchange and is generally considered as one of the important assets for the economic growth of the country;

WHEREAS, it has become decisive to primarily prevent and control animal diseases in order to maximize the benefits to be derived from this extensive livestock resource;

WHEREAS, the control of animal diseases requires the establishment of a system to control the movement of animals, animal products and by-products within, into and out of the country;

WHEREAS, it has become necessary, in general, to promote the export trade of animals, animal products and by-products by controlling animal diseases and by observing international agreements on animal health;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

### *PART ONE*
### *General Provisions*

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Animal Diseases Prevention and Control Proclamation No. 267/2002."

2. *Definition*

In this Proclamation unless the context requires otherwise:

1) "Minister" or "Ministry" means the Minister or Ministry of Agriculture, respectively;

፪· "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯(፩) የተመለከቱትን ማለት ሲሆን ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ሲባል የአዲስ አበባና የድሬዳዋ አስተዳደርንም ይጨምራል፤

፫· "እንስሳ" ማለት ለዚህ አዋጅ ዓላማ ሲባል የቤትና የዱር እንሳሳ ሲሆን እንዲሁም የባህር እንስሳትና ንብን ያጠቃልላል፤

፬· "የእንስሳት ውጤት" ማለት ሥጋና የሥጋ ውጤቶች፣ ወተትና የወተት ውጤቶች፣ እንቁላል፣ ማር፣ እንዲሁም ሚኒስቴሩ ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ሲባል የእንሳሳት ውጤቶች ብሎ የሚሰይማቸውን ሁሉ ያጠቃልላል፤

፭· "የእንስሳት ተዋጽኦ" ማለት ቆዳ፣ ሌጦ፣ ጠጉር፣ ላባ፣ ዝባድ፣ ቀንድ፣ ሰም፣ ሸሆና፣ አጥንት፣ ሞራና ከነዚህ የሚገኙትን መኖን እንዲሁም ሚኒስቴሩ ወደፊት ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ሲባል የእንስሳት ተዋጽኦ ብሎ የሚሰይማቸውን ሁሉ ይጨምራል፤

፮· "በሽታ" ማለት ማንኛውም በሚኒስቴሩ የተመዘገበ ወይም የሚመዘገብ የእንስሳት በሽታ ነው፤

፯· "ዓለም አቀፍ የእንስሳት ጤና ድርጅት" ማለት ኢትዮጵያ አባል የሆነችበትና በዓለም አቀፍ ደረጃ የእንስሳት በሽታዎችን ቁጥጥር ለማስተባበር የተቋቋመ ድርጅት ነው፤

፰· "ተዛማች የእንስሳት በሽታ" ማለት በእንስሳት ላይ ከፍተኛ እልቂት እና/ወይም በሽታ የሚያስከትል፣ ከእንስሳ ወደ ሰው የሚተላለፍ፣ ከባድ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳት የሚያደርስ ወይም በዓለም አቀፍ የእንስሳት፣ የእንስሳት ውጤቶችና ተዋጽኦዎች ንግድ ላይ ተጽእኖ የሚያደርስ የተመዘገበና ባስቸኳይ መገለጽ ያለበት ማንኛውም ተላላፊ የእንስሳት በሽታ ነው፤

፱· "ክትባት" ማለት የተዳከመ ወይም ሕይወት የሌለው የበሽታ መንስኤ ተዋህስያን ውጤት ሆኖ እንስሳትን ከበሽታዎች ለመከላከል ለጤነኛ እንስሳት የሚሰጥ ነው፤

፲· "ቁስ" ማለት ከበሽተኛ እንስሳት ጋር በሚኖረው ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ባልሆነ ንክኪ በመበከል በሽታን ማስተላለፍ የሚችሉ ማናቸውም የእንስሳት ጉዝጓዝ፣ መኖ፣ ግርግም፣ ውሃና የውሃ መጠጫ ገንዳዎች፣ በረቶች፣ ልዩ ልዩ የመገልገያ ቁሳቁሶች፣ ተሽከርካሪዎችና ሌሎች ከበሽታ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ነገሮች ያጠቃልላል፤

፲፩· "የባዮሎጂካል ውጤት" ማለት ሪኤጀንት፣ የደም ቅራሪ፣ የተዳከመ ወይም የሞተ ክትባትና የጀርም ጀነቲክ ውጤት ሆኖ የእንስሳት በሽታን ለመመርመር፣ ለመከላከልና ለማከም ተግባር የሚውል ነው፤

፲፪· "የፓቶሎጂካል ናሙና" ማለት የተፈጥሮ ሂደትን ያል ተከተለ የሴል እድገት ወይም በበሽታ አስተላላፊ ወይም ተህዋስ ወይም ጥገኛ ከተበከለ ወይም መበከሉ ከተጠ ረጠረ ሕይወት ካለው ወይም ከሞተ እንስሳ ተወስዶ ለምርመራ ወደ ላቦራቶሪ የሚላክ ነገር ነው፤

፲፫· "ተሕዋስ ማስወገድ" ማለት ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ በበሽታ አስተላላፊ ተሕዋስ ወይም ጥገኛ የተበከለን ቁስ በሚገባ ካጸዱ በኋላ ፀረ ተሕዋስ በመጠቀም የበሽታ መንስኤዎችን የማስወገድ ተግባር ነው፤

፲፬· "የአስተዳደር ባለሥልጣን" ማለት በብሔራዊ ክልላዊ መስተዳድሮች በማናቸውም ደረጃ ሕዝቡን ለማስተ ዳደር የተመረጠ ኃላፊ ነው፤

፲፭· "የእንስሳት ጤና ተቆጣጣሪ" ማለት የእንስሳት በሽታን ለመቆጣጠር በሚኒስቴሩ ወይም በክልል መስ ተዳድሮች የተመደበና ኃላፊነት የተሰጠው የእንስሳት ጤና ባለሙያ ነው፤

፲፮· "የእንስሳት ጤና ባለሙያ" ማለት በየደረጃው የሚሰ ጠውን የእንስሳት ሕክምና ትምህርት ተከታትሎ ዲግሪ፣ ዲፕሎማ ወይም ሰርቲፊኬት ያለው ሙያውን ለመተ ግበር የተፈቀደለት ነው፤

2) "Region" means any of those Regional States specified under Article 47(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and for the purpose of this Proclamation includes the Addis Ababa and Dire Dawa Administrations;

3) "Animal" means for the purpose of this proclamation domestic and wild animals includs sea animals and bees;

4) "Animal Product" means meat and meat-products, milk products, egg, honey and any other animal products to be designated as animal products by the Ministry for the purpose of this Proclamation;

5) "Animal by-product" means hide, skin, hair, feather, musk, horn wax, hoof, bone, tallow and animal feed derived from these and includes also all other products designated as such by the Ministry for the purpose of this Proclamation;

6) "Disease" means any animal disease registered or to be registered by the Ministry;

7) "Office International des Epizooties (OIE)" means the international animal health organization, established for the purpose of co-ordinating, the control of animal disease of which Ethiopia is a member;

8) "Noticeable Disease" means all contagious animal diseases which are characterized by high mortality and/or high morbidity or zoonotic nature or which causes serious socio-economic losses and/or affects international trade of animals, animal-products and by products, and which should be registered and notified immediately;

9) "Vaccine" means a suspension of attenuated or killed pathogenic micro-organisms to be administered to healthy animals for the prevention of animal diseases;

10) "Fomite" means bedding materials, animal feeds or managers, water and watering troughs, stables, utensils, vehicles and other materials which have direct or indirect contact with sick animals and capable of spreading disease;

11) "Biological Product" means regents, sera, attenuated or killed vaccines and mirobial genetic material used for the diagnosis, prevention and treatment of animal disease;

12) "Pathological Sample" means Tumer or material obtained from live or dead animals, containing or suspected of containing infectious or parasitic agents, to be sent to a laboratory;

13) "Disinfection" means the application after thorough cleaning, of procedures intended to destroy the infectious or parasitic agents of animal diseases, from fomites which may have been directly or indirectly contaminated;

14) "Administrative Officer" means an administrator appointed for public administration at any level in regional governments;

15) "Animal Health Officer" means an animal health professional assigned and authorized by the Ministry or by Regional Governments to control animal diseases;

16) "Animal Health Professional" means one who has pursued veterinary education and has been awarded degree, diploma or certificate and permitted to practice his profession;

፲፯· "የእንስሳት ጤና ተጠሪ" ማለት በእንስሳት ጤና አጠባበቅ መሠረታዊ የእንስሳት ጤና ክብካቤ ሥልጠና የተሰጠው የገበሬ ማኅበር፣ የኅብረት ሥራ ማኅበር ወይም የአርብቶ አደሩ ማኅበረሰብ የእንስሳት ጤና ተወካይ የሆነ ሰው ነው፤

፲፰· "የእንስሳት ጠባቂ" ማለት የማንኛውም እንስሳ ባለቤት የሆነ ወይም ለእንስሳው ኃላፊ የሆነ ማንኛውም ሰው ነው፤

፲፱· "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፳· "የኳራንቲን ጣቢያ" ማለት እንስሳትን እንደአስፈላጊነቱ ለተወሰነ ጊዜ አግልሎ በማቆየት፣ ከሌሎች እንስሳት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ እንዳይገናኙ በማድረግ ጤንነታቸውን በመከታተል እንዲሁም እንዳስፈላጊነቱ፤ የክትባት ምርመራዎችንና ሕክምና ለማካሄድ አስፈላጊ የሆኑ መሰናዶዎችን ያሟላ የተለየ ሥፍራ ነው፤

፳፩· "የመውጫ ወይም የመግቢያ መቆጣጠሪያ ጣቢያ" ማለት ለዓለም አቀፍ ትራፊክ ክፍት የሆነ ማንኛውም ዓለም አቀፍ የአውሮፕላን ማረፊያ ወይም የባህር ወደብ፣ የየብስ ወይም የባቡር የወሰን ጣቢያ ነው፤

፳፪· "ዓለም አቀፍ የሳኒተሪ የምስክር ወረቀት" ማለት ለሰው ምግብነት፣ ለእንስሳት መኖ ወይም ለሌሎች ተግባሮች የሚውሉ የእንስሳት ውጤቶችና ተዋጽኦዎች ጥራትና ሀይጂን ዓለም አቀፍ ደረጃን የጠበቀ መሆኑን በማረጋገጥ በላኪው አገር የእንስሳት ጤና አገልግሎት የሚሰጥ ወይም የገዥውን አገር ፍላጎት ያሟላ የምስክር ወረቀት ነው፤

፳፫· "ዓለም አቀፍ የእንስሳት ጤና የምስክር ወረቀት" ማለት ወደ ውጭ ሀገር የሚላኩ እንስሳትን፣ የእንስሳን አባለዘር፣ ጽንስና የለማ እንቁላልን ጤንነትና ደህንነት መርምሮ በማረጋገጥ በላኪው አገር የእንስሳት ጤና አገልግሎት የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ነው፤

፳፬· "የእንስሳት ጤና አገልግሎት አስተዳደር ጽ/ቤት" ማለት በየደረጃው በፌዴራልና በክልል የእንስሳት በሽታን ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር፣ ክትባትና ሕክምና ለመስጠት፣ በተጨማሪም ሌሎች የእንስሳት ጤና ነክ ሥራዎችን ለመሥራት የተቋቋመ አካል ነው።

## ክፍል ሁለት
## የእንስሳት በሽታዎችን ስለመከላከልና መቆጣጠር

### ፫· የእንስሳት በሽታ መከሰቱን ስለማሳወቅ

፩· የእንስሳት በሽታ ሲከሰት የእንስሳት ጠባቂው ወዲያውኑ በአካባቢው ለሚገኝ የእንስሳት ጤና ተጠሪ ወይም የአስተዳደር ባለሥልጣን ወይም ለእንስሳት በሽታ ተቆጣጣሪ በቃልም ሆነ በጽሁፍ የማሣወቅ ግዴታ አለበት።

፪· ማንኛውም የእንስሳት ጤና ባለሙያ በሥራው ላይ እያለ ተዛማች የእንስሳት በሽታ መኖሩን ሲያረጋግጥ ይህንኑ በአስቸኳይ በአቅራቢያው ለሚገኝ የእንስሳት ጤና አገልግሎት አስተዳደር ጽ/ቤት ማሳወቅ አለበት።

፫· የእንስሳት ጤና ተቆጣጣሪው ሪፖርት የተደረገለት የእንስሳት በሽታ መኖሩን ለማረጋገጥ አስፈላጊውን ማጣራት በማድረግ በሽታው መኖሩን ሲያረጋግጥ ለሚመለከተው የእንስሳት ጤና አገልግሎት አስተዳደር ጽ/ቤት ወዲያውኑ ሪፖርት ማድረግ አለበት።

፬· የእንስሳት በሽታ ስለመከሰቱ ሪፖርት የተደረገለት ክልልም በአፋጣኝ ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ማድረግ ይኖርበታል።

፭· ሚኒስቴሩም ስለተከሰተው ተዛማች የእንስሳት በሽታ በዓለም አቀፍ የእንስሳት ጤና ድርጅት አማካይነት ለሌሎች አገሮች መረጃ እንዲደርስ ያደርጋል።

፮· የእንስሳት ጤና ተቆጣጣሪው የእንስሳት በሽታ በአካባቢው ሲከሰት ሪፖርት የሚደረግበትን ሥርዓት ለመከታተልና የሚወሰዱ እርምጃዎችን ለማቀናጀት በግንባር ቀደምትነት ኃላፊነትና ተጠያቂነት አለበት።

17) ''Animal Health Representative" means a person trained in basic animal health care and who represents a Peasant Association or Co-operative or pastoralist community in animal health;

18) "Custodian" means any person who is an owner of any animal or who is in charge of such animal;

19) "Person" means natural Person or juridical entity having legal personality;

20) 'Quarantin Station" means a place where animals are kept isolated for a specified period from other animals, as may be necessary, to follow-up their health, and be given vaccination and examination, as may be necessary;

21/ "Entrance or Exite post' means any international airport or any sea port, road or railway station check point, at the boundary demarcation line, open to international traffic;

22) "International Sanitary Certificate" means a certificate issued by the veterinary authority of the exporting country certifying that the products and by-products of animal origin destined for human or animal consumption or other purposes comply with recognized international standards or the interests of the buyer/ importer country for its quality and hygiene;

23) "International Animal Health Certificate" means a certificate issued by the vererinary administration of the exporting country certifying the state of good health of animals, semen, embryo/ova, and hatching-eggs destined for export;

24) "Animal Health Service Administration Office' means an office established, at the Federal and Regional level, for the prevention, control of animal diseases and to carry out vaccination as well as other treatments related to animal diseases.

## PART TWO
## *Prevention and Control of Animal Diseases*

### 3. *Notification to be given upon outbreak of Animal Disease*

1) The custodian of an animal shall immediately notify verbally or in writing the occurrence of animal disease to the nearest veterinary animal health representative, administrative officer or animal health officer.

2) Every animal health professional, who in the course of his work or practice discovers the existence of a noticeable disease, shall forthwith report the matter to the nearest veterinary administration.

3) The animal health officer after being notified shall take steps as may be necessary for the purpose of ascertaining the existence of the said disease and on being satisfied that such disease exists, shall promptly make a reprot to the concerned veterinary administration.

4) The region so notified the occurrence of noticeable disease shall forthwith report to the Ministry.

5) The Ministry shall make the information available to other countries through the Office International Des Epizootic (OIE) concerning the occurrence of noticeable disease in the country.

6) The animal health officer shall have the primary responsibility and accountability to follow up the already established reporting system and accordingly to co-ordinate the measures to be taken whenever animal disease outbreak occurs in his surrounding.

፯· የእንስሳት ጤና ተጠሪ እና የአስተዳደር ባለሥልጣን ለዚህ አዋጅ ተግባራዊነት አስፈላጊውን የመፈፀም ግዴታ አለባቸው።

፰· የተዛማች የእንስሳት በሽታዎች ዝርዝርና ስለሚገለጹበት ሁኔታ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ ይገለጻል።

፬· <u>የእንስሳት በሽታ የገባባቸውን አካባቢዎች የማሳወቅ ሥልጣን</u>

፩· ሚኒስቴሩ አንድ አካባቢ ተዛማች የእንስሳት በሽታ የተከሰተበት መሆኑን በሕዝብ መገናኛ እንዲገለጽ ያደርጋል።

፪· ማስታወቂያውም በሽታው ያለበትን ሥፍራና አለ የተባለውን የበሽታ ዓይነት እንዲሁም መወሰድ የሚገባቸውን እርምጃዎች ለይቶ የሚገልጽ መሆን አለበት።

፫· ሚኒስቴሩ በሽታው ተከስቶበታል የተባለውን አካባቢ ስፋት እንደበሽታው ስርጭት ሁኔታ መጨመር፣ መለወጥ ወይም መቀነስ ይችላል።

፭· <u>የእንስሳት በሽታ የተከሰተባቸውን አካባቢዎች ስለሚመለከቱ ጉዳዮች</u>

፩· የእንስሳት ጤና ተቆጣጣሪው በጽሁፍ ካልፈቀደ በስተቀር የእንስሳት በሽታ ከገባበት አካባቢ እንስሳት፣ የእንስሳት ውጤቶችና ተዋጽኦዎች ወደ ሌላ ሥፍራ መጓጓዝ አይኖርባቸውም።

፪· በሽታ አለበት በተባለ ሥፍራ ላይ የሚገኙት እንስሳት ሁሉ በተቻለ መጠን ከሕዝብ መተላለፊያ መንገድ ርቀው መጠበቅ ይኖርባቸዋል።

፫· የእንስሳት ጤና ተቆጣጣሪው በሽታው አለበት በተባለው ሥፍራ የሚገኘን ማንኛውንም በእንስሳት በሽታ የተያዘን ወይም መያዙ የተጠረጠረን እንስሳ እንዲለይና ተስማሚ ነው ብሎ የሚያምንበትን ምልክት ሊያደርግ ይችላል።

፬· በሽታው አለበት በተባለው ሥፍራ ዙሪያ ለሚገኙ እንስሳት እንዳስፈላጊነቱ የከበባ ክትባት እንዲሰጥ ይደረጋል።

፭· በእንስሳት በሽታ ታመው የሞቱ ወይም በበሽታ መያዛቸው የተጠረጠሩ እንስሳት በድን የእንስሳት ጤና ተቆጣጣሪው በሚሰጠው ትዕዛዝ መሠረት መወገድ ይኖርበታል።

፮· <u>የእንስሳት በሽታ የተከሰተበት አካባቢ ከበሽታ ነጻ መሆኑ የሚገለፅበት አኳኋን</u>

፩· ተዛማች የእንስሳት በሽታ አለበት ተብሎ ማስታወቂያ የወጣበት አካባቢ በሚኒስቴሩ ከበሽታው ነፃ ነው ተብሎ እስካልተገለጸ ድረስ ከበሽታው ነፃ እንደሆነ አይቆጠርም።

፪· በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬(፩) መሠረት የእንስሳት በሽታው ተዛምቶበታል የተባለ አካባቢ ከበሽታው ነፃ መሆኑ በሚኒስቴሩ ሲረጋገጥ ሚኒስቴሩ ቀደም ሲል በሽታው መኖሩን ባስታወቀበት መንገድ አካባቢው ከበሽታው ነፃ መሆኑን ያሳውቃል።

፯· <u>የእንስሳት በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ስለሚወሰዱ እርምጃዎች</u>

በማናቸውም ወቅትና ቦታ የእንስሳት በሽታዎች እንዳይከሰቱና እንዳይዛመቱ እንደአስፈላጊነቱ ሚኒስቴሩ እና/ወይም ጉዳዩ የሚመለከተው ክልል፤

፩· የእንስሳት በሽታ መኖሩ ከተረጋገጠበት ወይም ከተጠረጠረ አካባቢ ወይም አገር፣ እንስሳት፣ የእንስሳት ውጤት፣ የእንስሳት ተዋጽኦ እና ቁስ ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል።

፪· የእንስሳት በሽታ መኖሩ ከተረጋገጠበት ወይም ከተጠረጠረ ክልል እንስሳት፣ የእንስሳት ውጤቶች፣ የእንስሳት ተዋጽኦዎች እና ቁስ ወደ ሌላ ክልል እንዳይዘዋወሩ ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል።

፫· የእንስሳት በሽታዎችን ለመከላከል እንስሳት፣ የእንስሳት ውጤቶችና ተዋጽኦዎች አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎችን ሳያሟሉ ድንበርን አቋርጠው እንዳይዘዋወሩ ይቆጣጠራል።

፬· ኢትዮጵያ የገባችባቸውን ዓለም አቀፍና አህጉራዊ የእንስሳት ጤና ስምምነቶች በሀገሪቱ ውስጥ እንዲከበሩ ያደርጋል።

7) The animal health representative and the administrative officer are responsible to carry out the necessary measures for the proper implementation of this proclamation.

8) The list of noticeable animal diseases and the procedure for their notification shall be disclosed by a regulation issued pursuant to this Proclamation.

4. *Authority to Declare Areas Infected with Animal Disease*

1) The Ministry is authorized to declare an area being infected by noticeable animal disease through public media.

2) The notice shall specifically indicate the infected area, the type of disease and measures to be taken.

3) The Ministry may extend, diminish or otherwise alter the limit of an area declared as an infected area.

5. *Provisions Applying to Areas Infected by Animal Disease*

1) No animal, animal products and by-products shall be removed from an infected area without the written permission of the animal Health Officer.

2) All animals in such areas shall be herded as far away as possible from public roads.

3) In an area where animal disease exists, the animal health officer may isolate any animal infected or suspected of being infected with animal disease and brand with marks he deems appropriate.

4) Ring vaccination shall be carried out as deemed necessary to animals in the infected areas.

5) The carcasses of animals infected or suspected of being infected with animal disease shall be disposed of in accordance with the instruction given by the animal health officer.

6. *Declaration of an Infected Area Free from Animal Disease*

1) An area which has been declared infected by noticeable disease, shall not be considred free from the disease until it is declared free by the Ministry.

2) An area which has been declared to be an infected area pursuant to Article 4(1) of this Proclamation would be declared as free by the Ministry in the same manner in which it was declared infected, after the disease has been completely put under control.

7. *Measures for the Prevention and Control of the Spread of Animal Disease*

In order to prevent the occurrence and the spread of animal diseases at any time and place, the Ministry and/or the concerned region, as the situation requires, shall:

1) Prohibit and Control and the importation of animals, animal products, animal by-products, and fomites from areas or countries infected or suspected of being infected by animal disease.

2) Prohibit and Control the movement of animals, animal products, by-products, and fomite from regions infected or suspected of being infected by animal disease to other regions in the country.

3) Control and regulate the movement of, with out having ful filled the required preconditions, animals, animal products and by-products across border in order to prevent the spread of animal diseases.

4) Cause international and regional animal health agreements, to be respected within the country, to which Ethiopia is a signatory.

፭· ከሰው ወደ እንስሳትና ከእንስሳት ወደ ሰው የሚተላለፉ በሽታዎችን ለመቆጣጠር ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ይሠራል፣
፮· ከዱር እንስሳት ወደ ቤት እንስሳት፣ ከቤት እንስሳት ወደ ዱር እንስሳት፣ የሚተላለፉ ተዛማች የእንስሳት በሽታ ዎችን ለመቆጣጠር አስፈላጊ የሆኑ የመከላከያ እርምጃ ዎችን ይወስዳል፣
፯· ለእንስሳት፣ ለእንስሳት ውጤቶችና ተዋጽኦዎች ኢምፖር ተሮች፣ ኤክስፖርተሮች፣ አምራቾች፣ ተመጋቢዎችና በአ ጠቃላይም ለኅብረተሰቡ በየጊዜው ስለእንስሳት በሽታዎች ሁኔታ አስፈላጊውን መረጃ ይሰጣል፣
፰· የእንስሳት በሽታዎች እንዳይስፋፉና ባዕድ በሽታዎች ወደ አገሪቱ እንዳይገቡ የአጣዳፊ ጊዜ ዝግጁነትና የበሽታ ክትትል ሥርዓት ይዘረጋል፣
፱· የእንስሳት በሽታዎች በኅብረተሰቡ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖ ሚያዊ እና ጤና ላይ የሚያደርሱትን ጉዳት መሠረት በማድረግ ቅደም ተከተል በማውጣት የቁጥጥር ፕሮግራም ያካሂዳል፣
፲· አገሪቱን ደረጃ በደረጃ ከተዛማች የእንስሳት በሽታዎች ነጻ ለማድረግና የአገሪቱን የእንስሳት፣ የእንስሳት ውጤቶችና ተዋጽኦዎች የውጭ ንግድን ለማስፋፋት ከበሽታ ነጻ የሆኑ ቀጣናዎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን እንዲቋቋሙ ያደርጋል።

፰· <u>የእንስሳት ጤና ተቆጣጣሪ ሥልጣን</u>

የእንስሳት በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር፣ የእን ስሳት ጤና ተቆጣጣሪ፣

፩· የመከላከያ፣ የህክምና ወይም እንደአስፈለጊነቱ የኳራ ንቲን እርምጃዎችን ተግባራዊ ለማድረግ እንስሳትን የመመርመር፣
፪· እንስሳት ከመጓጓዛቸው በፊት፣ በመጓጓዝ ላይ እንዳሉ፣ ከተጓጓዙም በኋላ የመመርመርና እንዲሁም እንዳስፈላ ጊነቱ ዝውውራቸውን የመቆጣጠር፣
፫· እንስሳት፣ የእንስሳት ውጤቶችና ተዋጽኦዎች ወይም የእንስሳት መኖ የሚገኙባቸውን ማናቸውም ቅጥር ግቢ ወይም አካባቢ ገብተው የመመርመር፣
፬· የእንስሳት በሽታን ለመለየት ሲባል ከማንኛውም እንስሳ፣ የእንስሳት ውጤቶች ወይም ተዋጽኦዎች ናሙና የመውሰድ፣
፭· አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በማንኛውም ወቅት እንስሳት እንዲመረመሩ፣ እንዲከተቡ፣ እንዲታከሙ፣ በፀረ ተባይ መድሃኒት እንዲረጩ ወይም በኳራንቲን እንዲቆዩ የማድረግ፣
፮· እንስሳት እንዲለዩ፣ እንዲታረዱ ወይም እንዲወገዱ ትእዛዝ የመስጠት፣
፯· በመግቢያና በመውጫ የመቆጣጠሪያ ጣቢያዎች ተገቢውን ቁጥጥር የማድረግ፣
፰· የሞቱ እንስሳት በድን፣ የበድን ቅሪቶች፣ የተበላሹ የእንስሳት ውጤቶች፣ በእርድ ወቅት የሚወዳድቁ ቅንጥ ብጣቢዎች፣ አዛባ፣ እበት እና ጉዝጓዝ በተገቢው ሁኔታ መወገዳቸውን የመከታተል፣
፱· ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት ሳይወሰን የእንስሳት ጤና ተቆጣጣሪው የእንስሳት ህክምና ሙያ አስፈላጊ የሚያደ ርጋቸውን ሌሎች እርምጃዎች የመውሰድ፣

ሥልጣን ይኖረዋል።

፱· <u>ስለ እንስሳት ጤና መረጃ ልውውጥ</u>

፩· የእንስሳት በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር፣ ውጤታማ የሆኑ የበሽታ ቁጥጥር ፖሊሲና ስልቶችን ለመንደፍ፣ አገሪቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚጠበቅባትን ግዴታዎች ለመወጣት ሚኒስቴሩ አገር አቀፍ የእንስሳት ጤና የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት ይዘረጋል።
፪· ሚኒስቴሩ በየጊዜው በዓለም አቀፍ ደረጃ በእንስሳት ሕክምና ሳይንስ በኩል የሚገኙትን አዳዲስ ውጤቶች በሙያው ለተሰማሩ ግለሰቦችና ድርጅቶች ያሳውቃል።
፫· ተዛማች የእንስሳት በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆ ጣጠር እያንዳንዱ ክልላዊ መንግሥት ከአጎራባች ክልሎችና ከሚኒስቴሩ ጋር አስፈላጊ መረጃዎችን መለዋወጥ ይኖርበታል።



5) Work in close collaboration with the Ministry of Health in order to control zoonotic diseases.
6) Take necessary preventive measures to control the transmission of noticeable diseases from domestic animals to wild animals and from wild animals to domestic animals.
7) Keep informed, importers, exporters, producers, consumers and the general public, of animals, animal products and by-products about animal disease situation in the country.
8) Establish an emergency preparedness and epidemic-surveillance system to contain the spread of animal diseases and avoid the introduction of exotic diseases into the country.
9) Set priorities for the control of animal diseases based on their socio economic and public health impact and implement control programms.
10) Establish disease free zones with concerned bodies to free the coutnry, step by step, from noticeable diseases and promote the export of animals, animal products and by-products.

8. *Powers of Animals Health Officer*

In order to prevent and control animal diseases, an animal health officer shall have the power to:

1) inspect animals and apply prophylactic, therapeutic treatments or necessary quarantine measures as required;
2) inspect animals prior to transport, during transport and after transport, limit or prohibit their movement if so required;
3) enter and inspect any premise or area where animals, animal products, animal by-products or animal feed are kept;
4) take samples from any animal, animal products or by-products for the purpose of identifying animal disease;
5) require at any time, animals to be examined, vaccinated, treated, sprayed with anti pest or undergo a period of quarantine if he considers it necessary;
6) order isolation, slaughter or disposal of animals;
7) carry out appropriate inspection at entrance and exit posts.
8) supervise the safe disposal of dead animals, parts thereof, contaminated animal products, wastes obtained at slaughter, dung, manure and litter;
9) Take all other necessary veterinary measures as required, without being restricted to the above mentioned.

9. *Exchange of Animal Health Information*

1) In order to prevent and control animal diseases, to formulate effective policy and strategies for disease control and to execute the country's international obligation the Ministry shall establish a national animal health information system.
2) The Ministry shall disseminate current animal health scientific findings to those persons and organizations engaged in animal health activities.
3) In order to prevent and control noticeable animal diseases, each regional government shall exchange necessary information with neighbouring regional governments and the Ministry.

## ክፍል ሶስት
### ፲ የእንስሳት፣ የእንስሳት ውጤቶችና ተዋጽኦዎች ዝውውር

**የኳራንቲን ጣቢያዎች ስለማቋቋም እና ስለመቆጣጠር**

፩· የኳራንቲን ጣቢያ እንስሳትን ለማቆየትና ለማጓጓዝ በሚያመች ቦታ ላይ አስፈላጊ የሆኑ መሰናዶዎችን አሟልቶ መቋቋም ይኖርበታል።

፪· የኳራንቲን ጣቢያዎች ስለሚቋቋሙባቸውና ስለሚያሟሊቸው መስፈርቶች በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ ይወስናል።

፫· ሚኒስቴሩ፣ የሚቋቋሙ የኳራንቲን ጣቢያዎችን ከሚሰጠው የእንስሳት ጤና አገልግሎት አንጻር ይቆጣጠራል፤ እንደ አስፈላጊነቱም ሥልጣኑን ለክልሎች በውክልና ይሰጣል።

**፲፩· የመውጪያ እና የመግቢያ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎችን ስለማቋቋም**

፩· ሚኒስቴሩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ሆኖ እንስሳት፣ የእንስሳት ውጤቶችና ተዋጽኦዎች ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡበትን፣ ከሀገር ውስጥ ወደ ውጭ የሚወጡበትን የመውጪያ እና የመግቢያ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች ይወስናል።

፪· ከተዛማች የእንስሳት በሽታዎች ቁጥጥርና ከበሽታ ነፃ የሆኑ ቀጣናዎችን ከማቋቋም አንጻር እንስሳት፣ የእንስሳት ውጤቶችና ተዋጽኦዎች ከክልል ወደ ክልል አግባብ ካላቸው ክልሎች ጋር በመሆን ይወሰናል።

**፲፪· እንስሳት፣ የእንስሳት ውጤቶችንና ተዋጽኦዎችን ወደ ውጭ ሀገር ስለመላክ**

፩· ወደ ውጭ አገር የሚላኩ እንስሳት በቅድሚያ ኳራንቲን ጣቢያ ውስጥ ገብተው ለተወሰነ ጊዜ እንዲቆዩ መደረግ አለበት።

፪· ወደ ኳራንቲን ጣቢያ የሚገቡት እንስሳት ተዛማች የእንስሳት በሽታ ካልተከሰተበት አካባቢ የመጡና የዝውውር ፈቃድ ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል።

፫· እንስሳት፣ የእንስሳት ውጤትና ተዋጽኦዎችን ወደ ውጪ ሀገር ለመላክ የሚያጓጓዙ ሰዎች የማጓጓዣ መስፈርቶችን ጠብቀው ማጓጓዝና እንዲሁም የተሰየሙትን የመውጪያ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች መጠቀም ይኖርባቸዋል።

**፲፫· እንስሳት፣ የእንስሳት ውጤቶችና ተዋጽኦዎች ወደ ሀገር ውስጥ ስለማስገባት**

፩· ማንኛውም ሰው እንስሳትን፣ የእንስሳት ውጤቶችና ተዋጽኦዎችን ወደ ሀገር ውስጥ ከማስገባቱ በፊት በቅድሚያ ስለሚገቡት እንስሳት፣ የእንስሳት ውጤቶችና ተዋጽኦዎች ዓይነትና ዝርያ፣ ብዛት፣ የመጓጓዣ ሁኔታ፣ የመድረሻ ቀን የመግቢያ በር እንዲሁም ከየት ሀገር እንደሚመጡ የሚያቋርጧቸውን ሀገሮች ለሚኒስቴሩ በማሳወቅ የመግቢያ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተፈቀደላቸው እንስሳት፣ የእንስሳት ውጤቶችና ተዋጽኦዎች ሲገቡ በመግቢያ ጣቢያ ላይ በእንስሳት ጤና ተቆጣጣሪዎች መታየት ይኖርባቸዋል።

**፲፬· ዓለም አቀፍ የእንስሳት ጤናና የሳኒተሪ የምስክር ወረቀት**

፩· ማናቸውም እንስሳ፣ የእንስሳ አባለዘር፣ ጽንስ፣ የለማ እንቁላል፣ የእንስሳት ውጤቶች የእንስሳት ተዋጽኦዎች ሲገቡ በመግቢያ ጣቢያ ላይ በእንስሳት ጤና ተቆጣጣሪዎች መታየት ይኖርባቸዋል።

፪· የእንስሳት ጤናና የሳኒታሪ የምስክር ወረቀቶች ሊይዟቸው ስለሚገቡ ዝርዝሮች በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

**፲፭ የእንስሳት የዝውውር ፈቃድ**

፩· ማንኛውም ሰው እንስሳትን ከወረዳ ወደ ወረዳ እና/ወይም ከክልል ወደ ክልል ለማዘዋወር ከእንስሳቱ መነሻ ቦታ ከበሽታ አንፃር ፈቃድ መያዝ ይኖርበታል።

፪· የሚሰጠው የእንስሳት የዝውውር ፈቃድ የእንስሳቱን መነሻና መድረሻ ቦታ፣ የጉዞ አቅጣጫ፣ የእንስሳቱን ዓይነትና ብዛት፣ የእንስሳቱን የጤንነት ሁኔታና ሌሎች አስፈላጊ ዝርዝሮችን የሚገልጽ መሆን ይኖርበታል።

## *PART THREE*
### *Movement of Animals, Animal products and By-products*

**10. Establishment and Supervision of Quarantine Stations**

1) A quarantine station shall be established with necessary facilities in an isolated and suitable area for keeping and transporting animals.

2) Conditions and requirements of quarantine stations shall be determined by regulations to be issued pursuant to this Proclamation.

3) Pertaining to animal health service, the Ministry shall inspect established quarantine stations, and if rquired delegate its power to regions.

***11. Establishment of Entrance and Exit Posts***

1) The Ministry may decide with concerned bodies on the establishment of entrance and exit posts through which animals, animal products and by-products exit or enter the country.

2) For the purpose of controlling noticeable diseases and establishment of disease free zones, the Ministry, as deemed necessary, may decide with the concerned regions to establish check-posts to control the movement of animals, animal products and by-products from one region to another region.

***12. Export of Animals, Animal Products and By-Products,***

1) Animals for export shall be kept in a quarantine station for specified period.

2) Animals kept in a quarantine station for export purpose, must originate from an area free from noticeable animal diseases and must be accompanied by movement permit.

3) Persons who transport export animals, animal products and by-products should comply with transport requirements and use designated exit posts.

**13. *Importation of Animals, Animal Products and By-Products***

1) Any person shall obtain an entrance permit by applying to the Ministry stating the type of product, country of origin, quantity, means of transport, date of arrival, port of entry and transit countries prior to importation of animals, animal products and by-the products.

2) Animals, animal products and by-products imported in accordance with Sub-Article (1) of this Article shall be checked at the port of entry by the animal health officer.

***14. International Animal Health and Sanitary Certificates***

1) Any animal, semen, embryo, hatching-eggs, animal products, animal by-products, biological products and pathological samples to be exported or imported shall be accompanied by recognized international animal health or sanitary certificate.

2) Details to be included in the certificates shall be determined by the regulations to be issued pursuant to this Proclamation.

***15. Animals Movement Permit***

1) Any person shall obtain animals movement permit with respect to animal disease, from the animals' place of origin to transport animals from Woreda to Woreda and/or from region to region.

2) The animals movement permit to be issued shall indicate the animals' place of origin, destination, route, type and number of animals, health status and other necessary details.

## ክፍል አራት
## ስለ እንስሳት ጤና ባለሞያዎች ምዝገባና አገልግሎት አሰጣጥ

፲፮· ምዝገባ

፩· የእንስሳት ጤና ባለሞያ ካልተመዘገበና የምዝገባ ምስክር ወረቀት ካላገኘ በስተቀር በእንስሳት ጤና ጥበቃ ሥራ ላይ መሠማራት አይችልም።

፪· ሚኒስቴሩ ያልተመዘገቡ የእንስሳት ጤና ባለሙያዎችና ሌሎች ባለሙያ ያልሆኑ ተጠቃሚዎች ሊያከናውኗቸው ስለሚችሉ የእንስሳት ጤና አገልግሎት ሥራዎች መመሪያ ያወጣል።

፫· የእንስሳት ጤና ባለሞያዎችን ለመመዝገብና ፈቃድ ለመስጠት የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች ምክር ቤት ይቋቋማል።

፬· ምዝገባው ስለሚካሄድበትና የእንስሳት ጤና ባለሞያዎች ምክር ቤት ስለሚቋቋምበት ሁኔታ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

፲፯· የእንስሳት ጤና አገልግሎት ስለመስጠት

፩· ማንኛውም ሰው አስፈላጊዎቹን መስፈርቶች አሟልቶ እስከቀረበ ድረስ የእንስሳት ጤና አገልግሎት መስጫ ጣቢያ፣ ማዕከል ወይም ተቋም ማቋቋም ይችላል።

፪· ማንኛውም ሰው ለእንስሳት ጤና አገልግሎት ጣቢያ፣ ማዕከልና ተቋም የንግድ ሥራ ፈቃድ ለማግኘት በቅድሚያ ከሚኒስቴሩ ወይም ጉዳዩ ከሚመለከተው ክልል የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማቅረብ ይኖርበታል።

፫· ሚኒስቴሩ የግል የእንስሳት ጤና አገልግሎት እንዲስፋፋ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል።

፬· ሚኒስቴሩ እንደየአገልግሎቶቹ ባህርይ የመንግሥትና የግሉ ዘርፍ የእንስሳት ጤና አገልግሎት የሚኖራቸውን ሚናና ኃላፊነት ይለያል።

## ክፍል አምስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፲፰· ስለ ካሣ

፩· የእንስሳት በሽታ እንዳይዛመት ለመከላከልና ለመቆጣጠር በእንስሳት ጤና ተቆጣጣሪው ትዕዛዝ መሠረት የታመመ እንስሳ የተወገደ ወይም የታረደ ከሆነ ለጠባቂው ምንም ዓይነት ካሣ አይከፈልም።

፪· በእንስሳት ጤና ተቆጣጣሪው ትዕዛዝ መሠረት የእንስሳው በድን እንዲቀበር ወይም እንዲቃጠል ከተደረገ የበድኑ ማስወገጃ ወጪ ለጠባቂው አይከፈልም።

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ላይ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ተዛማች የእንስሳት በሽታን ከመላ ሀገሪቱ ወይም ከተወሰነ የሀገሪቱ ክፍል ለመከላከልና ለመቆጣጠር እንዲቻል ሚኒስቴሩ እንስሳት እንዲታረዱ ወይም እንዲወገዱ ትእዛዝ ከሰጠ እንደአስፈላጊነቱ ካሣ የሚከፈልበትን ሁኔታ ያመቻቻል።

፬· በኳራንቲን ጣቢያ ውስጥ በተዛማች የእንስሳት በሽታ መከሰት ምክንያት ለሚታረዱት እንስሳት ካሣ አይከፈልም።

፭· የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) አፈጻጸም የሚረዳ እና ባለሙያው በእንስሳት ጤና አገልግሎት ሥራ ላይ እያለ ለሚደርስበት ጉዳት ስለሚከፈል ካሣ ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

፲፱· የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም የሚመለከተው ሰው ይህን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን ተግባራዊ ለማድረግ መተባበር ይኖርበታል።

፳· የአገልግሎት ክፍያ ስለመሰብሰብ

ሚኒስቴሩ ለሚሰጠው አገልግሎት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ መሠረት ክፍያዎችን ይሰበስባል።

፳፩· ቅጣት

ይህን አዋጅና በአዋጁ መሠረት የሚወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን የተላለፈ ማንኛውም ሰው በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት ይቀጣል።

## *PART FOUR*
## *Registartion of Animals Health Professionals and Delivery of Services*

16. *Registration*
   1) No animal health professional shall practice veterinary profession unless he is registered and obtained registration certificate.
   2) The Ministry shall issue directives concerning animal health interventions which may be performed by unregistered animal health professionals and other non- professional users.
   3) A veterinary council shall be established for the registration and licensing of animal health professionals.
   4) Conditions for the registration and establishment of the council shall be determined by a regulations to be issued pursuant to this Proclamation.

17. *Animal Health Services Delivery*
   1) Any person may establish animal health station, center or institution upon the fulfillment of the necessary requirements.
   2) Any person shall in advance produce a certificate of competence from the Ministry or concerned region in order to obtain a business license of animal health station, center or institution.
   3) The Ministry shall create favorable conditions for the promotion of private animal health services delivery.
   4) The Ministry shall, based upon the nature of the services, define the role and responsiblites of the public and the private sector in the delivery of animal health services.

## *PART FIVE*
## *Miscellaneous Provisons*

18. *Compensation*
   1) No compensation shall be paid to the custodian if deseased animal is killed or slaughtered for the purpose of prevention and control of the spread of animal disease based on the instruction of the animal health officer.
   2) When the carcass of a dead animal is buried or burned upon the instruction of the inspecting officer, no expense of disposal shall be paid to the custodian.
   3) without prejudice to Sub- Articles (1)and(2) of this Article, if the Ministry gives order for the slaughter or removal of animals in order to prevent and control noticeable animal diseases in the whole or part of the country, the Ministry may arrange for compensation as deemed necessary.
   4) No compensation shall be paid for animals slaugtered because of occurrence of noticeable animal desease in the quarantine stations.
   5) The Council of Ministers may issue a regulation for the implementation of Sub- Article (3) of this Article and having regard to compensation to injuries incurred by professionals engaged in animal health service rendering activities.

19. *Duty to Co-operate*

Any concerned person shall co operate for the implementation of this Proclamation and regulations and directives to be issued pursuant to it.

20. *Collection of Service Fee*

The Ministry may collect fees for the services rendered in accordance with the regulation to be issued by the Council of Ministers.

21. *Punishment*

Any person who violates the provisions of this Proclamation, regulations and directives issued pursuant to it shall be punished under the provisions of the Penal Code.

፳፪· የተሻሩና ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች

፩· የከብት በሽታዎችን ስለመከላከል የወጣው አዋጅ ቁጥር ፩፻፸፩/፲፱፻፶፫ በዚህ አዋጅ ተሽሯል።

፪· ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

፳፫· ደንብና መመሪያ ስለማውጣት

፩· የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለአዋጁ አፈጻጸም የሚረዱ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።

፪· ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚረዱ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

፳፬· አዋጁ የሚጸናበት ቀን

ይህ አዋጅ ከጥር ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ጥር ፳፫ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት



*22. Repealed and Non- applicable Laws*

1) Animal Diseases Control Proclamation No 171/1961 is repealed by this Proclamation.

2) No Proclamation, regulations and directives which is inconsistent with this Proclamation shall have no effect with respect to matters governed by this Proclamtion.

*23. Issuance of Regulations and Directives*

1) The Council of Ministers may issue regulations necessary for the proper implementation of this Proclamtion.

2) The Ministry may issue directives for the proper implementaion of this Proclamation and regulations issued under this Proclamation.

*24. Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 31st day of January, 2002

Done at Addis Ababa, this 31st day of January,2002.

***GIRMA WOLDEGIORGIS***

***PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA***

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE